የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የኮ/መ/ቁ 269450

ቀን 02/10/2013 ዓ/ም

ዳኛ፡- ዘላላም ተስፋዬ

ይግባኝ ባይ፡- የሃረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ጠበቃ ዚያድ ሬድዋን ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

ለፍርድ መነሻ የሆነው ተጠሪ በሀረሪ ክልል ህገመንግስት ከአንቀፅ 48-52 ስር በተደነገገው አግባብ ለሃረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ለመመረጥ የሚያበቁ መስፈርቶች በመጣስ ከህግ አግባብ ውጭ ክልሉን ሲመራው የነበረው የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ወደ ብልፅግና ፓርቲ ውህደት መፍጠሩን ተከትሎ አገር አቀፍ ፓርቲ የሆኑት ብልፅግና ፓርቲ እና ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ በክልሉ ለ6ኛ ጠቅላላ ምርጫ ዕጩዎችን ማቅረባቸው ህጋዊነት የለውም በማለት አመልካች ለጀጎል ምርጫ ክልል ፅ/ቤት ቅሬታ ያቀረበ መሆኑን አመልካች ባቀረበው ቅሬታ ላይ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሰረት መርምሮ በ5(አምስት)ቀናት ውስጥ ውሳኔው ሳይወስን በተደጋጋሚ ጉዳዩ እንዳስቸገራቸው በመግለፅ ቅሬታችንን እየተመለከቱት መሆኑን በመግለፅ እጃቸው ላይ አቆይተው ለሃረሪ ክልል ምርጫ ቦርድ ቅ/ፅ/ቤት በዚሁ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲያስተላለፍ መልሶ የላከው ቅሬታችንም እንዲፈታ ለመልስ ሰጭ ብናቀርብም አቅጣጫ እናስቀምጣለን በማለት ይህ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ውሳኔ አልተሰጠበትም በሚል በአዋጅ ቁጥር 1162/2013 አንቀፅ 153(8) አግባብ መሰረት ይግባኙ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበ መሆኑን የይግባኝ ቅሬታ አቤቱታው ያስገነዝባል፡፡

መልስ ሰጭ በይግባኝ ባይ የቀረበለትን የቅሬታ አቤቱታ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ በእጁ አስቀምጧል በሚል የመልስ ሰጭን ውሳኔ ባለመስጠት የወሰነው ውሳኔው በመቃወም ይግባኝ ባይ ግንቦት 06 ቀን 2013 ዓ.ም አሻሽሎ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ሲሆን የይባኝ ቅሬታዎችም ባጭሩ፡-

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የሃረሪ ክልል ምክር ቤት 36 አባላት ያሉትና በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የክልል ምክር ቤት የተደራጀ መሆኑን በመግለፅ የመጀመሪያው ጉባኤ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ የሚባል ሲሆን 22 አባላት ያሉትና ሁለተኛው ጉባኤ ደግሞ የሃረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚባል እና 14 አባላት ያሉት መሆኑን በማውሳት ይህ ሁለተኛው የሃረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የተባሉት የክልሉ ተወካዮች በተሻሻለው በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከአንቀጽ 49-50 ድረስ እንደተደነገገውም ሆነ በባለፉት አምስት ምርጫዎች በፓለቲካ ድርጅት ወይም በግሉ እጩ ተወዳዳሪ ፓርቲነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑ በተረጋገጠ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ በዚሁ አግባብም በብሐየሰረቡ የተደራጁ እንደ የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ለብሔረሰቡ ህግ ወጭ እና በህገመንግስቱ የተረጋገጡ መብቶችን ለማስከበር በጉባኤው ሲወሳደርና ሲወከሉ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ወደ ብልጽግና መዋሃዱን ተከትሎ ክልሉን እያስተዳደረው ፓርቲ ብልጽግና ፓርቲ ነው፡፡ በመሆኑም በሃረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት መሰረት ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ተወካይ ሊሆን የሚገባው እጩ አንድም በግል የብሐየረሰቡ ተወካይ አሊያም በብሔረሰቡ የተደራጁ የብሔሩ ፓርቲዎች እጩ ወኪል ብቻ ለምርጫ ውድድር ምዝገባ መደረግ እየጠገባ እያለ ይህንኑ በሚቃረን መልኩ አገር አቀፍ ፓርቲዎች የሆኑት የብልጽግና ፓርቲ እና ነፃነትና እኩልነት በክልሉ ለሐረር ብሐየራዊ ጉባኤ ዕጩ አቅርበው ማስመዝገባቸው ህጋዊ ተቀባይነት የለውም በዕጩነት መቅረብ እና መልስ ሰጭ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ እንዲዘረዝ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የይግባኝ ባይ ቅሬታን ከመዝገቡ ግልባጭ ጋር አዋዶ የይግባኝ ቅሬታውን በሰማበት ቀን ከለያቸው ነጥቦች አኳያ በመመርመር ሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ተብሎ በተለየው የክልሉ ተወካዮች ላይ ሁለቱ አገር አቀፍ የተሻሻለው ህገ መንግስትና ከኢትዮጵያ የምርጫ የፓለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አኳያ ብሎም ከሌሎች ተዛማጅ ህጎች አንጻር ተገቢነቱን ለመመርመር የይግባኝ ባይ የይግባኝ ቅሬታ አቤቱታ የሚያስቀርብ ሆኖ ስለተገኘ መልስ ሰጭ በአድራሻው የይግባኝ ባይ ቅሬታና ያስቀርባል የተባለበት ነጥብ ደርሶት መልሱን በቀን 17/09/2013 በተጻፈ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

መልስ ሰጭ ባቀረበው መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፍሬ ነገር ረገድ ክርክሩን ያቀረበ ሲሆን ባጭሩ ያቀረበው ክርክር ስንመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ረገድ ያቀረባቸው ክርክሮች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 50(30)፣51(15) እና 55(1)(መ) ላየ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሐረሪ ክልል መንግስት የተሻሻለው ህገ መንግስት ከአንቀጽ 48 -



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

52 ያሉት የማቃረኑ በመሆኑና እንዲህ በሆነ ግዜ ህገ መንግስታዊ ጉዳይ ስለሚያስነሳ የማየት ስልጣን የለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከመሆኑ አኳያ ይህ ችሎት የማየት ስልጣን የለውም ፤

በእጩ አቀራረብ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ አቤቱታ በቅርንጫፌ ጽ/በት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በተሠጠ በሠባት ቀናት ውስጥ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ስላቀረበ በአዋጅ መሠረት ክሡ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ በመሆኑ ፣ የይግባኝ ባይ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሲሆን ፤

ያቀረበው ክርክር የምርጫ ክልል ቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ የይግባኝ ባይን ቅሬታ ለመቀበሉ ካሳየም ፣ ይህ ቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ እጩ አቀራረብን የተየየዘውን ቅሬታ የሚቀበልና የሚወሰን የበታች የምረጫ ክርክር ዳኝነት አካለ ስለሆነ ይግባኝ ባይ ለዚሁ አካል ቅሬታውን አቅርቦ አይመለከተኝም የሚል ምላሽ ሠጥታል ከማለት ባሻገር የተሠጠውን ምላሽ በተመለከተ ከአቤቱታው ጋር የተያያዘ ማስረጃ ስለሌለ በአዋጅ አግባብ አሞጦ ስርዓቱን ጠብቆ ለዚህ ችሎተ የቀረበ አይደለም የሚል ሲሆን ፣

በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረበው የፖለቲካ ፖርቲዎች በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ ተደራጅተው ከቦርዱ እውቅና የጋኙ ፖርቲዎች እንደሆኑ ፣ አደረጃጀታቸውም በአገር አቀፍ ፣ በክልልና ከክልል በታች በሆነ ደረጃ በምርጫ ተወዳድሮ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ በመሆኑ የብልጽግና ፖርቲ ና ነፃነትና እኩልነት ፖርቲዎች በሐረሪ ክልል ለመወዳደር የሚከለክል ህግ የለም ብለል፡፡ ይግባኝ ባይም የመልስ መልሡን በጽሁፍ በይግባኝ ያቀረባቸውን ቅሬታዎች አጠናክሮ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩና የክርክሩ አመጣጥና ይዘት ካለይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ከግራ ቀኙ ክርክር አኳያ እልባት ሊሠጥባቸው የሚገቡ ናቸው በሚል የሚከተሉትን ነጥቦች ለይቷል፡፡

1. በግራ ቀኙ መካከለ እየከራከረ ያለው መልስ ሠጭ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዳቀረበው ህገ መንግስታዊ ጥያቆ የሚያስነሳ ነው ወይ?

በይግባኝ የቀረበው አቤቱታ የቅሬታ ስርዓቱን ጠብቆ Exhaustion የኮ.መ.ቁ 259450 Rules አምጦ የቀረበ አይደለም ወይ ? በቅሬታ ስርዓቱ አግባብ በአዋጁ መሰረት የይግባኝ ባይ ቅሬታ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይ?

3) በፍሬ ጉዳዩ ላይ ሁለቱ አማር አቀፍ የሆኑት የብልጽግና ፓርቲ እና የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በአካራካሪው የምርጫ ጣቢያ እጩ ተመራጭ ሊያስመዘገቡ አይገባም ወይ? የሚሉ ናቸው፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከቀረቡት የመዝገቡ ግልባጭ ክርክሮችና አግባብ ካላቸው ህጎች አኳያ መዝገቡን መርምሯል፡፡ መርምሮ እንደተረዳውም በመጀመቲያ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል እያከራከረ ያለው ጉዳይ ህገመንግስታዊ ጥያቄ ያስነሳል ወይ? ይህ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ስልጣን የለውም ወይ? የሚለው ሲሆን ይግባኝ ባይ አጠንክሮ የሚከራከረው አገር አቀፍ ፒርቲዎች እጩ ተመራጭ ለሐረር ብሔራዊ ሊክ ሊያስመዘግቡ አይገባም፣ ሊሰረዙ ይገባል የሚል ከይዘቱ አንጻር አር አቀፍ ፓርቲዎች በሃረር ብሔራዊ ጉባኤ ምክር ቤት እጩ ለማስመዝገብ የለባቸወም የሚል የተነሳ በመሆኑና በአስረጂነትም የሐረር ክልል የተሻሻለው ህገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ‹‹የሐረር ብሔራዊ ጉባኤ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ በሌላ በኢትዮጲያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረር ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል›› የሚል በመሆኑና በሌላ አንጎ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 2(13) አንቀጽ 31 መሰረት አገር አቀፍ ፓርቲዎች ለክልል ፓርቲነት እስከተመዘገቡ ድረስ በክልሎች ለመወዳደር እንደሚችሉ ተደንግጎ እያለ ይህም ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 50(3)፣51(15) እና 55(መ) አኳያ ታሳቢ መደረግ እየተገባው፣ የሁለቱ ክልላዊና የፌዴራል አዋጆች (ህገመንግስቱ) ግልጽ ህገመንግስታዊ ተቃርኖ አለው የሚል ነው፣በዚህ የህገ መንግስታዊ ጥያቄ ትርጉም ረገድ ይህ ችሎት የመረመረው ሲሆን በዋናነት ዋናውን ፍሬ ጉዳይ ወደጊለኞች ጭብጥ ተመልክቶ እልባት ሲሰጥ ምን ያክል ግራቀኙ እየተከራከሩበት ያለው ጉዳይ ተገቢውን ፍሬ ጉዳይ እና የድንጋገዎች መንፈስ ለይቶ የማከል መሆኑን ላይ በተለይም በግራቀኙ አካራካሪው ነጥብ የህገ መንግስት ጥያቄ የሚያሳነሳ መሆኑና ወደፊት የምናየው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ይልቁንም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9(2) መሰረት የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባቸው የተመለከተ በመሆኑና ህገ መንግታዊ ትርጉም በማይጠይቁ ህገ መንግስቱ መሰረት አድርገው የሚነሱ ክርክሮች ተመልክተው ፍርድ ቤቶቹ ዳኝነት ሊሰጡ አይገባም የሚባልበት የህግ አምክንዮ ባለመኖሩና የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ ረገድ በሠ/መ/ቁ 207036 በቀን 19/09/13 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ የጎንዮሽ ትርጉም (obit diction) ያስቀመጠ ከመሆኑ አኳያ አከራካሪው ጉዳይ የህገ

መንግስታዊ ትርጉም የሚያስፈልገው ነው ብሎ ችሎቱ አላመነም ፡፡ ስለሆነም ችሎቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን አለው ተብሏል ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ ይግባኝ ባይ ያቀረበው አቤቱታ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ፣ የይርጋ ጊዜው ያግደዋል የተባሉ የተቀራኙ ጭብጦችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 153 ላይ በግልፅ እንደተመለከተው በጊዜ የተቀመጡ ስርዓቶች እንደተዘረጉ ያሳያል ፤ እነዚህ ስርዓቶች ላይ የተቀመጡ ጊዜያት በተመለከተ ለሐረሪ ክልል ጀጎል ልዩ ክልል ምርጫ ጣቢያ መጋቢት 12 ቀን 2013 ዓ.ም የይግባኝ ባይን ቅሬታ የተቀበለ መሆኑን ያሳያል፣ ቀጥሎም የሃረሪ ክልል ምርጫ ጣቢያም ቅሬታውን የተቀበለ መሆኑን የስር መዝገቡ ያስረዳል፡፡ እንግዲህ በዚህ ሂደት ሁሉ ይግባኝ ባይ በግልፅ የተሰጡ ውሳኔዎች ከመልስ ሰጭ የሉም በሚል ክርክር የሚያደርግ በመሆኑና እነዚህን ቅሬታዎች በምርጫ ቦርድ ተዋረድ ጽ/ቤት ስለመድረሱ ከቀረቡት ማስረጃዎች መገንዘብ የሚቻል ስለሆነ የምርጫ ቦርድ ምርጫ ጣቢያዎችም ሆነ ፣ የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታው የደረሳቸው ለመሆኑ እንጅ በአንፃሩ አቤቱታው ላይ ውሳኔያቸውን በጽሁፍ ያላሳወቁ ከመሆኑ አኳያ መልስ ሰጭም ውሳኔ ያሳረፈ ለመሆኑ ያልተከራከረ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ በተለይም ደግሞ የምርጫ ቦርድ በቀን 20/07/2013 ዓ.ም የይግባኝ ባይን አቤቱታ ተቀብሎ ያላስተናገደ መሆኑ ሲታይ አጠቃላይ ከአዋጅ አንቀፅ 153 መንፈስና ይዘት አኳያ እዚሁ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለመድረስ ከምርጫ ጣቢያው እስከ ከፍተኛው ፍርድ ቤት 30 ቀናት የሚያስፈልግ በመሆኑ በዚህ ችሎት ከቀረበው ጊዜ አንፃር ችሎቱ የቀረበውን የይርጋ ጊዜ አልተቀበለውም ፡፡ በተያያዘም በዚህ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ አቤቱታው በተዋረድ አለመቅረቡ መብትን የሚያሳጣ ድንጋጌም ሆኖ አልተገኘም ፡፡

በሌላ በኩል አቤቱታው ለምርጫ ቦርድ የቀረበ በመሆኑ የጊዜ አቆጣጠር ከፍ/ህ/ቁ 1851(ለ) ተመሳሳይ ትርጉም አኳያ የይርጋ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ክርክር ሆኖ አልተገኘም ፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ባይ በአዋጅ የተቀመጠውን የይግባኝ ቅሬታ ስርዓት አምጦ አልተጠቀመም/ Exhaust ton rule የሚለውን በተመለከተ የቀረቡት ማስረጃዎች ይግባኝ ባይ ስርዓቱን ጠብቆ ለችሎቱ ያቀረበ መሆኑን ስለሚያስረዱ እንደዚሁ በዚህ ረገድ የቀረበውን የመልስ ሰጭ ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በመጨረሻም አገር አቀፍ የሆኑት ብልጽግና ፓርቲ እና የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በአካራካሪው የምርጫ ጣቢያ ዘንድ እጩ ተመራጭ ሊያስመዘግቡ አይገባም ወይ? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ የመረመርነው ሲሆን፣ በመሰረቱ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው

ህገመንግስት አንቀጽ 50(2) "የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ውስጥና ወጭ በሌላ በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል ይላል ይህ በእንዲህ እንዳለ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ማንኛውም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚካሄድ ምርጫ መስፈርቱን የሚያማላ እስከሆነ ድረስ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በይግባኝ ባይ በኩል አጠንክሮ የሚከራከረው አገር አቀፍ ፓርቲዎች ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ዕጩ ሊያቀርቡ አይገባም የሚል ነው ይሁን እንጅ ከላይ ባየነው የተሻሻለው የሃረሪ ህገመንግስት ላይ የሰፈረው ቅድመ ሁኔታ እጩ ተመራጮች የሚወክሉበት ፓርቲ የሃገር አቀፍ ፓርቲ ሳይሆን በሐረሪ ክልል ደረጃ የተደራጁ ፓርቲዎች ብቻ መሆን እንዳለባቸው አያስገድድም፤ የክልሉ ፓርቲዎችን ብቻ እጩ ማቅረብ የሚችሉ የሚል ሆኖ ድንጋጌው አልተቀረፀም የተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ህገመንግስት አጽንኦት በድንጋጌው የሰጠው እጩ ተመራጩ የሐረሪ ብሔረሠብ መሆኑን እንጅ የሚወክለውን ፓርቲ አይደለም፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይግባኝ ባይ ሃገር አቀፍ ፓርቲ የሆኑት ብልጽግና ፓርቲ እና ነጻነት ለእኩልነት ፓርቲ እጩ ተመዝጋቢዎችን መልስ ሰጭ ሊሰረዝ ይገባል የሚለው ቅሬታው ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም ከዚህ ጋር ተቆራኝቶ መታየት ያለበት ይግባኝ ባይ የሁለቱን ፓርቲዎች አገር አቀፍ ፓርቲ ሆነው እጩ የማቅረባቸው ህጋዊነት እንጅ የቀረባቸውን እጩዎች ብሔረሠባዊ ማንነት ተንተርሶ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ባለመኖሩና ይልቁንም በይግባኝ ቅሬታውም ላይ የእጩዎች ብሔረሰብ ሃረሪ ቢሆንም እንኳን የሚል ከመሆኑ አኳያ የተጠየቀው ዳኝነት ተቀባይነት ያለው አይደለም ተብሏል ከዚህ ባለፈ ይግባኝ ባይ ሁለቱ አገር አቀፍ ፓርቲዎች ያስመዘገበችው እጩዎች የሐረሪ ብሔረሰብ ቢሆኑም እንኳን የሃረሪ ብሔር ጥቅም ሊያስጠብቁ አይችሉም በማለት ያቀረበው ክርክር በፍርድ ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ሳይሆን ብሔረሰቡ በሚስጥር በሚሰጥ ድምጽ (ምርጫ) የሚዳኙት ሆኖ ካልተገኘ የይግባኝ ባይን የይግባኝ ቅሬታ ችሎት አልተቀበለውም በሚል ፍድ ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

# ው ሳ ኔ

1. ይግባኝ ባይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በሚል መልስ ሰጭ ውሳኔ ባለመስጠት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ሊፀና ይባል በሚል ተወስኗል፡፡
2. ሁለቱ አገር አቀፍ ፓርቲዎች ማለትም የብልጽግና ፓርቲ እና የዕኩልነትና ነፃነት ፓርቲ ያስመዘገባቸው ዕጩዎች በህጉ አግባብ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ሊሰረዙ አይገባም በሚል ተወስኗል፡፡
3. ግራቀኙ ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ተብሏል መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ ተብሏል፡፡

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለው

ሳ/አ/ኤ/ቀ/ብ/ቱ/ሮ/መ/ሀ/ው/ት/አ/ቢ/ተ

ቀን 02/10/2013 ዓ/ም